# <u>መጋረጃው ያልተነሳ ተውኔት፣</u>
# <u>ያልተፈታ እንቆቅልሽ!</u>
# <u>የመንግሥቱ ኃይለማርያም የመጨረሻ ቀኖች!</u>

ክፍል ሁለት

በልጅግ ዓሊ

*በቅቡል አንደበት በቃላት ሞሽሮ፣*
*ወይም በልብ ወለድ በማስመሰል ፈጥሮ፣*
*ዓመኔታ እሚቀርጽ ምንም ይሁን የትም፣*
*ዕውነት እንደ ውሸት ብዙ መልክ የላትም።*

*አብርሃም በየነ*

<u>ካለፈው የቀጠለ</u>

*<< ጓድ ካሣ >> በቃለ መጠይቃቸው መንግሥቱን ከጄኔራሎች በላይ ጀኔራል ለማድረግ ስለ መንግሥቱ ማዕረግ ልብስ አንስተው ብዙ ባዝነዋል። መንግሥቱን ምን እሳቸው ቢክቡት በሕዝብ ዘንድና በታሪክ መነፅር ፈሪ፣ ነፍሰ ገዳይ ፣ ከሃዲና ራስ ወዳድ እንደነበረ በዓይናችን ያየነው እውነታ ነው።*

*የመንግሥቱ ኃይለማርያም መንግሥት የመጨረሻ ቀኖች ውስጥ የተፈጸመውን ስንገመግመው እስከ አሁን በኢትዮጵያ ታሪክ የሃገሪቱ መሪዎች አሳይተውት የማያውቁት ክህደት እንደሆነ እንረዳዋለን። የክህደቱ መፈጸም ብቻ ሳይሆን በአሁኑ ወቅት የደርግ ደጋፊዎች ይህንን አሳዛኝ ታሪክ በፈጠራ ተረት ተረት ለመቀየር የሚያደርጉት ጥረት ደግሞ የበለጠ የሚያሳዝን ነው። ምንም እንኳን መንግሥቱን <<እንደ ቆራጥ መሪ ፣ እንደ አፄ ዮሐንስ፣ እንደ አፄ ቴዎድሮስ>> ለመሳል ትልቅ ጥረት ቢደረግም በምንም መስፈርት መንግሥቱ ከከሃዲነት የሚያልፍ ስም ሊኖረው አልቻለም/ አይችልምም። ዛሬ የአደባባይ ምሥጢር የሆነው እውነት የሚያሳየን ይህ አረመኔ ለዓመታት የግል ጥቅሙን ለማስከበርና የሥልጣን ጥሙን ለማርካት ሲሮጥ እንደነበር ነው።*

*ብዙ ጸሐፊዎች የደርግ ወድቀት ከሶቭየት ኅብረት መፍረስ ቢያያይዙትም ለሻብያና ለወያኔ ሥልጣን መያዝ ትልቅ አስተዋጽዖ ያደረገው በግንቦት ወር በከፍተኛ መኰንንኖች ተጠንስሶ የነበረው መፈንቅለ መንግሥት መክሸፍ ነበር። ከዚያም ጋር በተያያዘ መኰንንኖቹ በግፍ በመጨፍጨፋቸው ምክንያት በሠራዊቱ ውስጥ የተፈጠረው የሞራል መላሸቅ ከፍተኛ ነበር። ከግድያው በኋላ የተፈጠረውን የሥልጣን ክፍተት የሞሉት የጦር መሪዎች ልምድ የሌላቸውና ከወያኔና ከሻዕብያ ጋር ከነበረው ፍልሚያ ይልቅ ሙስና ውስጥ በመዘፈቃቸው ለደርግ ውድቀት ከፍተኛውን አስተዋፅዖ አድርገዋል።*

*የዓሣ ግማቱ ከአናቱ እንዲሉ ይህ ንቅዘት ምንም እንኳን በሁሉም የመንግሥት መዋቅሮች ውስጥ ቢከሰትም <u>የመንግሥቱ ቤተሰባዊ ስብስብ</u> ውስጥ ጎልቶ ይታይ ነበር። በተለይ የመጨረሻው ሰዓት በደረሰ ጊዜ ተራ የሆነ ንግድ ውስጥ እንደተገባ ባለፈው መረጃዬን አንተርሼ አቅርቤለሁ። ይህ የቤተሰብ ኃይል ስለ ሃገር ደህንነት ከመደራደር ይልቅ ለግል የሚገኝ ንዋይን ማካበት ላይ አተኩሮ ነበር። ባለፈው በጥቂቱ ለማሳየት እንደ ሞከርኩት፣ ይህ ንቅዘት የጀመረው ቀደም ሲል ቢሆንም << ቆራጡ መሪያችን - ዳግማዊ ቴዎድሮስ >> በሚል ፕሮፖጋንዳ ታፍኖ ነበር። ለብዙዎቹም የፕሮፖጋንዳው ብዛት የተሠራውን ክህደት አለማመን ደረጃ ላይ አድርሷቸዋል። <<እሳቸው እንደ ቴዲ እዚሁ ነው ሽጉጣቸውን የሚጠጧት >> የሚለውን ተረት ዛሬም ድረስ የሚያምኑ አይጠፉም።*

*ውሸት ቢጋነን እውነት አይሆንምና ዛሬ እውነቱ አደባባይ ላይ ሲቀርብ ለዛ መልስ ከመስጠት አሁንም እንደበፊቱ ምክንያት እየተፈለገ በየቃለ መጠይቁና በሚጻፉ መጽሐፍት ከእውነት ሊሸሽ ይሞከራል። ሙሉውን << የጓድ ካሣ >> ቃለመጠይቅም ሆነ የመንግሥቱ <<ትግላችን>> መጽሐፍ ስንመለከት እውነትን እየቀለበሱ፤ ውሸትን በሕዝብ ውስጥ ለመከተብ የሚደረገው ጥረት አሁንም ከፍተኛ መሆኑን ያስገነዝበናል።*

*ከላይ እንደጠቀስኩት ይህ የመጨረሻው ሃገራዊ ክህደት በጣት የሚቆጠሩ ቤተሰባዊ አባላት ባሉት ቡድን ብቻ በድብቅ የተፈጸመ ነበር። ለዚህ ማስረጃው ብዙዎቹ የደርግ ባለሥልጣናት የመንግሥቱን ፕሮፖጋንዳ አምነው<<ቆራጡ መሪያችን ጥለውን አይሸሹም>>በሚል መፈክር ሥር በመሰባሰባቸው እየተንጋጉ ወያኔ እስር*

ቤት መታጎራቸው የሚታወቅ ነው። አንዳንዶቹ የደርግ ባለሥልጣናት እንዲያውም እሱ በፈረጠጠበት ዕለት ሃገራዊ ጉዳይን በሚመለከት ከእርሱ ጋር ቀጠሮ ነበራቸው። በዚህ ክህደት የተሳተፉት ግን ዛሬ በድሎት በምዕራብ ሃገሮች እየተንደላቀቁ ናቸው። ልብ ያለው ያስተውል !!!

ይህ የቤተሰብ ኃይል የንብረት ማሸሽንና የወደፊት የመኖሪያን ቦታ ዝግጅት ሲያደርግ የቆየ ለመሆኑ << ጓድ ካሣ ከበደ >> በሰጡት ቃለ መጠይቅ ይካዱት እንጂ እውነቱ ግን የአደባባይ ምስጢር ነበር። በቃለ መጠይቁ ውስጥ <<ከሚኒስትርነት ደረጃ ተነስቼ እስከ አሁን በማላውቀው ሁኔታ በአምባሳደርነት ወደ ጀኔቫ ተቀየርኩ>> የሚለው ንግግራቸው ከሁሉ የሚገርም ነው። እውን መንግሥቱ ኃይለማርያም << ጓድ ካሣ ከበደን>> ሳያማክር ይህንን ፈጸመ? ጀኔቭን የመሰለ ብዙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚገኙበት ቦታ ለተሻረ ሰው ነው የሚሰጠው?

በደርግ አገዛዝ ውስጥ ለሕዝብ ሽረት የሚመስል በውስጠ ታዋቂነት ሹመት የሆነ ዝውውር ለታማኝ <<ጓድ>> የሚሰጥ መሆኑ ግልጽ ነው። የዚህ ዓይነት አሠራር በደርግ ውስጥ የተለመደ መሆኑን በቀላሉ ማሳየት ይቻላል። በደርግ የመጨረሻ ዓመታት ውስጥ በሶቭየት ኅብረት የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩት የመንግሥቱ አጎት (ምን አልባት አሁን ሊካድ ይችላል) አሥራት ወልዴ ከሞስኮ ተቀይረው በዝምብባዌ አምባሳደር የተሾሙት መንግሥቱ ከመጥፋቱ ከዓመት በፊት ነበር። እንደሚታወቀው የሶቭየት ሕብረት አምባሳደር መሆን ከዝምብባዌ ጋር ሲወዳደር <<ሽረት>> መስሎ ይታያል። ግን እውነቱ ወደፊት ለታቀደው ክህደት የተደረገውን ቅድመ ዝግጅት በጉልህ የሚያመለክት ነው። የኢሠፓ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና የውጭ ግንኙነት አላፊው <<ጓድ ካሣ>> ይህንን አላውቅም ነበር ብለው ያስቁን ይሆን?

የአሥራት ወልዴ ዝውውር ከመንግሥቱ የወደፊት መኖሪያ ቦታ ዝግጅት ጋር የተያያዘ ነበር። መንግሥቱ ቀደም ብሎ ባለቤቱንና ልጆቹን ወደዚያው እንደላከ የአደባባይ ምሥጢር ነው። ይህ የሚያሳየን ይህ ክህደት የተጀመረው ገና ቀደም ተብሎ እንደነበርና በኤርትራ ውስጥ ያን ያህል ጦር እየተዋጋ በሚያልቅበት ወቅት ቤተሰባዊው ቡድን ንብረት ማሸሽን እንደጀመረ ነው። ለዚህ ምስክር መጥራትም አያስፈልግም። መንግሥቱ በነተስፋዬ ገብረኪዳን እንደ ከሃዲ ከተወገዘ በኋላ አስራት ወልዴን ከአምባሳደርነት ሥልጣን መሻራቸው የክህደቱ አንዱ አቀነባባሪ መሆናቸውን ያሳየናል። <<ጓድ ካሣ>> በጄኔቫም አምባሳደርነት ሹመትን ምክንያቱን አላውቀውም ብለው ያስተባብሉ እንጂ፤ ከአምባሳደርነታቸው ውጭ ለመንግስቱ የታማኝነት ተግባር ያከናውኑ እንደነበር ግልፅ ነው። የሹመቱን አስፈላጊነት ወደፊት የምንመለከተው ይሆናል።

መንግሥቱ ቤተ እስራኤሎቹን በመሸጥ የተገኘውን 35 ሚሊዮን ዶላር ለምን ይዞ እንዳልፈረጠጠ ብዙ ሰዎች ይጠይቃሉ። መልሱ Stephen Spector በጻፉት <<Operation Solomon: The Daring Rescue of the Ethiopian Jews >> – በተሰኘው መጽሐፍ ገጽ 133 ላይ በግልጽ ተቀምጧል።

> Why had Mengistu fled when he was only days away from a multimillion-dollar << incentive>>? << The noose became too close for comfort.>> Lubrani told me. << He was wealthy enough by that time. He had a farm waiting for him in Zimbabwe. All dictators have these things. I had this all lined up. According to one report, Mengistu was destitute when he left Ethiopia, and his uncle was seeking aid for him from embassies in Harare. In actuality however, he had looted everything of value that he could from the treasury room in the Jubilee palace, including the crown jewels, gold boxes, ivory tusks and state gifts. Mengistu reportedly arrived in Zimbabwe with $3 million and Sunday times noted that he had stashed away hundreds of millions of dollars in Swiss bank accounts. He later invested in real estate in Harare's affluent suburbs buying opportunely at a time when white residents were fleeing the country. The former Ethiopian president paid $1.3 million in cash for one property alone.
>
> ለምንድነው መንግሥቱ ይህንን ብዙ ሚሊዮን ብር ሳይቀበል ጥሎ የጠፋው? አጥማጁ በምቾት ለመኖር ዝግጁ ነበር። ሉብራኒ ብሎ ነገረኝ። በመቀጠልም መንግሥቱ በዚያ ወቅት በጣም ሃብታም ሆኖ ነበር። ምቹ የሆነ የእርሻ ቦታ ተዘጋጅቶለት ነበር። አምባገነኖች ሁሉ ይህንን ያደርጋሉ። አንድ ሌላ ዘገባ መንግሥቱ ምንም ሃብት ያልነበረውና አጎቱ ሃራሬ ውስጥ በየኤምባሲዎቹ ይለምንለት እንደነበር ተመዝግቧል። **ነገር ግን እውነቱ ከኢዮቤሊዩ ቤተመንግሥት የሃገሪቱን ንብረት በአጠቃላይ የነገሥታቱን ወርቅ ፣ የዝሆን ጥርስ ፣ የወርቅ ሳጥኖችና የመንግሥት ስጦታዎች የሆኑት ዘርፎ ሄዷል።** መንግሥቱ 3 ሚሊዮን ዶላር ይዞ እንደገባ ይታወቃል። በተጨማሪ (Sunday Times) በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር በስዊስ ባንክ ማካበቱን አጋልጧል። ይህንኑ ገንዘብ በኋላ ሃራሬ ውስጥ የሃብታም መኖሪያዎች አካባቢ ነጮች ሃገሪቱን ለቀው ሲወጡ አጋጣሚውን በመጠቀም ገዝቷል። የቀድሞው የኢትዮጵያ መሪ 1.3 ሚሊዮን ጥሬ ገንዘብ እንደከፈለ የተረጋገጠ መረጃ አለ።

ከዚህ ጽሁፍ እንደምንመለከተው መንግሥቱ በስዊስ ባንክ ብዙ ተቀማጭ ገንዘብ እንደነበረው ነው። ይህ ገንዘብ እንዴት እዚያ ሊሄድ ቻለ?<<ጓድ ካሣ ከበደ>> በጄኔቫ አምባሰደር በነበሩበት ወቅት እጃቸው በዚህ የሃገሪቱን ገንዘብ በማሸሽ ሴራ አለበት ወይ? የሚለውን ጥያቄ ራሳቸው ሊመልሱት ይገባል።

<<ጓድ ካሣ>> ስለመንግሥቱ አወጣጥ የማውቀውም ቢኖር <<የጓድ ሊቀመንበሬን>> መጽሐፍ ስለምጠብቅ አልናገርም በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብን አሁን እውነቱን እንዲጠብቅ በዚያውም ከልብ የሚወዱትን አለቃቸውንና ጓዳቸውን መንግሥቱን በመጽሐፍ ሽያጭ ለሚያገኘው ገቢ ነፃ ማስታወቂያ ሰርተው አልፈዋል። የመንግሥቱን መጽሐፍ የመጀመሪውን ክፍል ያነበበ መንግሥቱ አሁንም ውሸት የሆነ ተረት ተረት እንደጻፈ ይረዳዋል። አሁንም <<ዝንብም ገድዬ አላውቅም>> የሚለውን ቅጥፈት እንደ እውነት ቆጥረው የታሪክ ድልድይ እንሥራለን ብለው ለሚያምኑ የአረመኔው ፕሮፖጋንዲስቶች እውነት እንደ ውሸት ብዙ መልክ እንደሌላት ሊረዱት ይገባል።

ስለ መንግሥቱ ፍርጠጣ <<ጓድ ካሣ>> ይደብቁት እንጂ የክህደቱ ዝግጅትም ሆነ ስምምነቱ ዛሬ እድሜ በዛን ጊዜ ለተሳተፉ የውጭ ዜጎች ለሕዝብ ምሥጢር አይደለም። ከዝግጅቶቹ መሃል ካሣ ከበደ፣ አሥራት ወልዴና መንግሥቱ ቤተሰቦቻቸውን ቀደም ብለው ማሸሻቸው ግልጽ ነው። ገና በውጊያ ላይ የነበረው ጦር የራሱ ሕልውና አጠያያቂ በነበረበት ወቅት ገንዘብ ማሸሽ፣ ንብረት ማካበት፣ ከውጭ መንግሥታት ጋር የራስን ጥቅም በሚመለከት መዶለትን ተያይዘውት ነበር። በአዲስ አበባ መንገድ ላይ ስንት ጀብዱ የሠሩ የኢትዮጵያ ሠራዊት አባላት በየመንገዱ ሞራላቸው ተሰብሮ፣ የሚበሉት አጥተው በሚሰቃዩበት ወቅት መሪዎቹ ደግሞ የሚኖሩትን የተንደላቀቀ ኑሮ ነበር። ገና ብዙ ያልተመለሱ እንቆቅልሾች አሉ። አሁንም ቢሆን ሃቁን የኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ ይጠብቃል።

ከላይ በጠቀስኩት መጽሐፍ ውስጥ ገጽ 131 እንዲህ ይላል።

Monday , May 20: The <<Clean Kill>>

> Monday had barely begun, London time , when a momentous message reached Schneider and other American Jewish leaders there: Mengistu was about to flee. It arrived in the form of riddle. There is << a place down south where S.O.( someone ) will go and make a trip to visit a home of his ,>> the message said . He was << likely to go very soon >> and it maybe very short trip .>> The <<visitor>> would be Mengistu , who would leave Ethiopia the next day, and the place down was Zimbabwe.
>
> ሰኞ ማለዳ ጠዋት በለንደን አቆጣጠር ለሽናይደር፣ ለአሜሪካንና ለአይሁዳውያን ድርጅት መሪዎች አንድ ጠቃሚ የሆነ መልዕክት ደረሳቸው። መንግሥቱ ሊሸሽ ነው የሚለው በድብቅ መልክ የተጻፈ መልዕክት ነበር።
> ወደ ደቡብ አካባቢ አንድ ጎብኚ መኖሪውን ለመጎብኘት ሊሄድ ነው። በጣም በአስቸኳይ ሊሄድም ይችላል። ምን አልባትም በጣም አጭር ጉዞ ሊሆን ይቻላል። ጎብኚ የተባለው መንግሥቱ ሲሆን ወደ ደቡብ የተባለውም ዝምባብዌ ነበር።

ከላይ እንደምንመለከተው የመንግሥቱ መፈርጠጥ ቀድሞ የተዘጋጀ ነበር። ለኢትዮጵያውያን ድብቅ ይሁን እንጂ ይህንን ጉዞ ላዘጋጁት የውጭ ዜጎች ምሥጢርነት አልነበረውም። የሚገርመው ግን ይህንን ጉዳይ የሚያውቁት በጣም የተወሰኑ ሰዎች ብቻ መሆናቸው ነው። መንግስቱ ከፈረጠጠ በኋላ ተስፋዬ ገብረ ኪዳን ምንም ስለፈላሻዎች እንደማያውቅ በመጻሐፉ ተጠቅሷል። እንዲያውም እስራኤላውያኑና አሜሪካውያኑ ካሣ ከበደን ጠይቆ እንዲረዳ ለተስፋዬ ገብረኪዳንን ነግረውታል። ከላይ በጠቀስኩት መጽሐፍ ውስጥ የመንግሥቱን የመጨረሻ ሰዓት በሚመለከት ገጽ 133 እንዲህ ብሎ ሠፍሯል።

> Mengistu was fleeing in secrecy and deception. He had left Addis in a small DASH -6 plane with a about a dozen senior military officers on the pretext that they were going to observe the training of new recruits in south central Ethiopia. In midflight, however, Mengistu abruptly had the pilot change the itinerary and proceed to Nairobi instead. From there he boarded a commercial craft that took him to Zimbabwe and all or most of the officers who had flown with him went directly back to Ethiopia.
>
> መንግሥቱ በምሥጢርና በማታለል ነበር የኮበለለው። በሃገሪቱ ደቡብ በሚገኝ የወታደር ማሰልጠኛ የሚሰለጥኑ አዲስ ተቀጣሪዎችን ለመጎብኘት በሚል ሰበብ በዳሽ 6 በምትባል ትንሽ አውሮፕላን ደርዘን ከሚሞሉ ወታደራዊ ባለሥልጣኖች ጋር ነበር ጉዞውን የጀመረው። በጉዞው ማህል ሳይታሰብ ነበር መንግሥቱ የጉዞውን መስመር ቀይሮ ወደ ናይሮቢ እንዲሆን ያደረገው። ከዛም በንግድ አውሮፕላን ወደ ሃራሬ ጉዞውን ቀጠለ። ከእሱ ጋር የነበሩት ወታደራዊ ባለሥልጣኖች ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል።

ሁኔታውን በተከታተሉ የውጭ ሰላዮችና አምባሳደሮች እውነቱ ግልጽ ሆኖ በተጻፈበት በአሁኑ ወቅት፤ እነ ካሣ ከበደና አዲስ የውሸት ታሪክ እንጽፋለን እያሉ የሚጥሩ የታሪክ ድልድይ ገንቢ ነን ባዮች ፣ ሃቁን በማጣመም ለራሳቸው በሚመች አዲስ ታሪክ ለመጻፍ በመራወጥ ላይ ናቸው። የሃገራችን ታሪክ ከሕዝቧ በተሠረቀ ገንዘብ

በተገዙ ታሪክ አጣማሚዎች ቢጻፍም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ሃቁን በተለያየ መንገድ እንዲያውቀው መጣር የሃቀኛ ጋዜጠኞች ተግባር ነው። ለንዋይ ጥቅም ሲሉ ይህንን የክህደት ታሪክ ማጣመም ሃገራችንን መንግሥቱ ከገደላት በላይ መግደል ነው።

በዚህ ክህደት በበዛበት የደርግ ፍጻሜ ውስጥ የተሠሩትን አስከፊ ክህደቶች በሙሉ ለመዘርዘር ጊዜ ይጠይቃል። በተለይ የነጻ ፕሬስ ሰዎች ይህንን ሃቅ ጎልጉለው በማውጣት ለሕዝብ ዓይንና ጆሮ መሆን ይገባቸዋል። **35 ሚሊዮኑ ዶላር የት ደረሰ የሚለው አሁንም መልስ ያስፈልገዋል?**

ከዓመታት በፊት << ጓድ ካሣ>> ጦቢያ በሚል መጽሄት ላይ በሰጡት ቃለ መጠይቅ በትክክል እንኳን መጥቀስ ባልችልም እስራኤሎች አንድ እምነት እንዳላቸው ተናግረው ነበር። <<የአንድ ይሁዳዊ ነፍስ ያዳነ ሕይወቱ ትድንለታለች>> የሚል ነበር። አዎ ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ ። ዛሬ <<ጓድ ካሣ>> ከሚኖሩት የተቀማጠለ ሕይወት አንጻር ስንመለከተው ትክክል ናቸው። ግን ደግሞ ሰው ለገንዘብ ብቻ አይኖርም። የአዕምሮ እርካታንም ይሻል። በተለያየ ወቅት ይህንን የውሸት ተረት ተረት እነ መንግሥቱ ቢተርኩና የአዕምሮ እረፍት ያገኙ ቢመስላቸውም የንጹሐን ደም ደግሞ በሌላ በኩል ይረብሻቸዋል።

መፍትሄው አንድ ነው! እውነትን ተናግሮ መገላገል ነው። አለበለዚያ ግን ሃቅ እየተከተለች ትነዘንዛለች። ታሪክም እውነቱን ከትቦ ማስቀመጡ አይቀርም።

ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስብ በሰላም ይክረም!

በልጅግ ዓሊ

Beljig.ali@gmail.com